// # የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 286 ጥቅምት 22 2006 ገጽ 1

> ግንቦት 7 ንቅናቄ ዛሬም እንደሁሌው ለነዚህ ወገኖች ኑ ተቀላቀሉን የሚል ጥሪውን ያቀርባል። ሁላችንም ከነክብራችን ሆነን ሰዎችን ሳይሆን ውዲቱን ሀገራችንና ህዝባችንን በፈቃደኝነት በነጻነት የምናገለግልበት ጊዜ እየቀረበ ነው፡፡
>
> ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ ፍትሻ ባህርዳርንና ኗሪዎቿን አማረረ

የዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ካድሬዎች፤ ፖሊሶችና የጸጥታ ሀይሎች ለግዜዉ ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት በባህርዳር ከተማ ዉስጥ ከፍተኛ ፍተሻ እያካሄዱ መሆኑን ባህርዳር ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሳበት ድምጽ ዘጋቢዎች በስልክ በላኩልን ዜና ገለጹ። በተላይ ከሳምንቱ መግቢያ እስከ ሳምንቱ አጋማሽ በነበረዉ ግዜ ዉስጥ በከተማዋ መውጪያና መግቢያ በሮች ላይ የጸጥታ ሀይሎች ተሳፋሪዎችን ከአዉቶቡሶችና ከግል መኪናዎች ዉስጥ በግድ ጎትተዉ እያወረዱ ጥብቅ ፍተሻ እንዳደረጉባቸዉ ለማወቅ ተችሏል። አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይህንን የወያኔ በድንገት የመጣ ፍተሻ ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ ከግዜ ወደ ግዜ እየተባባሰ ከመጣዉ የአማጽያን እንቅስቃሴ ጋር ሲያያይዙት ሌሎች ደግሞ በቅርቡ አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ዉስጥ የደረሰዉን አይነት የቦምብ ፍንዳታ ከወዲሁ ለመከላለክ ነዉ ይላሉ፤ ሆኖም እንዚህ ወገኖች አገዛዙ ለምን ባህርዳር ላይ እንዳተኮረ የሰጡት ምንም አይነት ምክንያት የለም።

የጸጥታ ኃይሎቹ በሚያካሂዱት ፍተሻ ባህርዳርና አካባቢዋ ዉስጥ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ስራና ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች የተስተጓጓሉ ሲሆን ህዝቡም በከፍተኛ ደረጃ እየተንገላታ መሆኑን የከተማዋ ነዋሪዎች በመናገር ላይ ይገኛሉ። የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ ለመፈጸም ለማያስባቸዉ ጭፍጨፋዎች ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት እንዲህ አይነት እርምጃ መዉሰዱ የተለመደ ነዉ ያሉት አንድ ስማቸዉ እንዲገለጽ ያልፈለጉ ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣን ይስ የሰሞኑ የባህርዳር ፍተሻ ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ አገዛዙን በማስጨነቅ ላይ ያለዉን

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በረከት ስምኦን የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ቦርድ ኃላፊነቱን ቦታ ለሬድዋን ሁሴን አስረከበ

የወያኔዉ ፓርላማ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ኃላፊነት ያቀረበዉን ሹመት ተቀብሎ ማጸደቁ ተሰማ። ይህ አንቅልፋምና ከአገዛዙ የቀረበለትን ነገር ሁሉ ከማጽደቅ ዉጭ ሌላ ምንም አይነት አማራጭ እንዳለዉ እንኳን የማያዉቀዉ ፓርላማ የኢትዮጵያን ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ለረዥም ጊዜ በቦርድ ኃላፊነት የመራዉ በረከት ስምኦን በሬድዋን ሁሴን እንዲተካ የቀረበለትን ጥያቄ እንዳለ ተቀብሎ አጽድቋል። ሹመቱ በአማካሪዎችም ሆነ በካቢኔ ደረጃ ምንም አይነት ዉይይት ሳይካሄድበት በድንገት የተደረገ ሲሆን በዚሁ ሬድዋን ሁሴን በሚመራዉ ቦርድ ዉስጥ በቅርቡ ለረዥም ጊዜ ካገለገለበት የብሮድካስት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኃላፊነቱ ተነስቶ በጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት የሕዝብ ተሳትፎ አደረጃጀት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ የሆነው የተሾመዉ ደስታ ተስፋውና አማኑኤል አብርሃም፤ ዓቢይ መሐመድ ከሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል፣ አቶ ገበየሁ በቀለ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ዶ/ር አብዲሳ ዘርዓይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አባል፣ መጋቢ ዘሪሁን ደጉ ከእምነት ተቋማት ፣ አቶ ዘርዓይ አስገዶም ከኢቲቪ የቦርዱ አባላት በመሆን ተሹመዋል። የፓርማዉ አባልና በተሰናባቹ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ በአባልነት ያገለገሉ አንድ ስማቸዉ እንደነገር ያልፈለጉ ግለሰብ የፓርላማዉን ሹመቱን አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት ሹመቱ ግልጽነት የጎደለው መሆኑን በመጥቀስ ማብራሪያ እንዲሰጣቸዉ ጠይቀዋል። እንደእሳቸው አባባል ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተጠሪ የሆኑ የመንግሥት የሚዲያ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት መሆናቸውን በማስታወስ ለሁለቱ ተቋማት 4ኛው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሹመት መስጠቱን አስታውሰዋል። ይህንኑ ማብሪያያ ይሰጠኝ በሚል ከፓርላማዉ የተነሳዉን ጥያቄ የፓርላማዉ አፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ጠ/ሚኒስትሩ በማንኛውም ጊዜ ሚኒስትሮችን ሲያነሱ ማብራሪያ እንደማይጠየቁ ሁሉ የቦርድ አባላትንም ሲሰየሙ ማብራሪያ ለመስጠት እንደማይገደዱ በመናገር አግባብ ያለዉን ጥያቄ በተለመደዉ የቃላት መዶሻዉ ደብድቦት አልፏል።

## ደብረማርቆ ዩኒቨርስቲ ዉስጥ ለተነሳዉ አመጽ የዩኒቨርሲቲዉ አስተዳደር ኢሳትን መኮነኑ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አዲስ ያወጣዉን ፀረ ህዝብ መመሪያ ተከትሎ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አዲስ የአለባበስ ፤ የአመጋገብና የአምልኮ ስርዓት ህግ ማውጣቱን በመቃወም የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች የረሃብ አድማ መጀመራቸዉን የዩኒቨርሲቲዉ አስተዳደር ገለጸ። ከዚህ በተጨማሪ አዲስ ከወጣዉ መመሪያ ዉጭ ዩኒቨርሲቲዉ ለተማሪዎች የመደበዉ የምግብ ፍጆታ መጠን እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነዉ በሚል የተማረሩት የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች አመጽ መጀመራቸዉን የዩኒቨርሲቲዉ ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ መናገራቸዉ ታዉቋል። ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ከዚሁ ጋር አያይዘዉ እንደተናገሩት ተማሪዎቹን ቁርስ፣ ምሳና እራት ለመመገብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተፈቀደው የቀን በጀት 12 ብር ብቻ ነዉ ካሉ በኋላ በደብረ ማርቆስ ከተማ 12 ብር ከአንድ ሻይና ዳቦ በላይ መግዛት እንደማይችል ተናግረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢሳት ቴሌቪዥን ያናገራቸዉ አንዳንድ የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች ደብረ ማርቆስ ዉስጥ ለአንድ ተማሪ በቀን 12 ብር ለምግብ መመደብ ተማሪዎችን በረሃብ ለመጨረስ ከመሞከር ተለይቶ አይታይም ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲዉን ተማሪዎች ጥያቄ ትክክለኛነት ያረጋገጡት የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ከመንግስት ፈቃድ ውጭ በሚልየን የሚቆጠር የበጀት ድጎማ እያደረግን ተማሪዎችን ለመመገብ ጥረት አድረገናል ብለዋል። ይህንን ሀቅ ሳይደብቁ የተናገሩትና የተማሪዎቹን ችገር በሚገባ የተረዱት ዶ/ር ንጉሴ የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የኢትዮጵያ ህዝብ ለመለስ ፋውንዴሽን ጆሮዉንም እዩንም አንደነፈገ ታወቀ

የህወሀት መስራችና የረጂም ግዜ መሪ የነበረዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት በተለየ በስምንት ወሩ ባለፈዉ መጋቢት መጨረሻ ላይ ይፋ ሆኖ የተመሰረተዉ የመለስ ፋውንዴሽን ከህዝብ ያገኛል ተብሎ የተገመተዉን የገንዘብ መዋጮ የሩቡን ግማሽም አለማግኘቱን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በሰልክ ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገለጹ፡፡ በመለስ ፋውንዴሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 781/2005 መንግስታዊ ተቋም ሆኖ የተመሰረተው ይህው ፋውንዴሽን ቤተመጻህፍትና ሙዚየም ለማቋቋም በማሰብ ሕዝቡ ገንዘብ እንዲያዋጣ በየቀኑ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ቅስቀሳ ከተጀመረ ከአምስት ወራት በላይ ቢቆጠርም እየተዋጣ ያለው ገንዘብ እጅግ አነስተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

ህዝብ በያለበት ለመለስ ፋዉንዴሺን የገንዘብ መዋጮ ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነዉ ፋውንዴሽኑን በበላይነት የምትመራዉና የሙስናዋ እመቤት በመባል የምታወቀዉ አዜብ መስፍንና ሚቹ ባለቤቷ ከህዘብ ዘርፈዉ በውጪ አገር ባንኮች ከፍተኛ ገንዘብ ማከማቻታቸዉን ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንና በውጪ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኋን በተደጋጋሚ በመዘገባቸዉ እንደሆን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛው የመንግስት ሰራተኛና የግሉ ዘርፍ ለህዳሴዉ ግድብ ገንዘብ እያዋጡ መሆናቸዉና ህዝቡ መለስ ዜናዊን ለመሰለ ሃያ አንድ አመት ሙሉ ለረገጠዉ ጨቋኝና ከፋፋይ ሰዉ የገንዘብ መዋጮ ማድረግ ባለመፈለጉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። የአዲሰ አበባ ምንጫችን ጨምሮም እንደገለጸዉ መዋጮው በውዴታ በባንክ ገቢ የሚደረግና ለጋሹ ስሙን ከማስመዝገብ በላይ መስጠትና አለመስጠቱ የማይታወቅ በመሆኑ ከፍተኛ የግንባሩ ካድሬዎችና ራሳቸውን የኢህአዴግ ደጋፊ ባለሃብቶች ነን የሚሉት ሳይቀሩ ለመዋጮው እጃቸውን አለመዘርጋታቸው መረጃው ያሳያል።

## በደቡብ ክልል የመምህራን ተቃውሞ እየተስፋፋ ነው

በደቡብ ክልል የሚገኙ መምህራን አባይ ወንዝ ላይ ለሚሰራዉ የህዳሴዉ ግድብ ማሰሪያ ካላዋጣችሁ በሚል ያለነሱ ፈቃድና ፍላጎት ከመስከረም ወር ደሞዛቸው ላይ ተቆርጦ የተወሰደዉ ገንዘብ ካልተመለሰልን በሚል የጀመሩት ተቃውሞ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች እየተስፋፋ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ደቡብ ክልል ጨንጫ ወረዳ ዉስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ"የተቆረጠው ደሞዛችን" ካልተመለሰ ስራ አንሰራም በሚል የተጀመረዉ የመምህራን ሰራ ማቆም አድማ ወደ ምእራብ አባያ ወረዳ ዘልቆ በመግባት በዚያም የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን " የተቆረጠብን ደመወዝ የማይመለስ ከሆነ ስራ አንሰራም በሚል " ብለዉ ለወረዳዉ ባልስልጣናት መናገራቸዉ ታዉቋል። የወረዳው አስተዳዳሪ፣ የድርጅት ጉዳይ ሃላፊና የወረዳው የመምህራን ማህበር ተወካይ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## በወያኔ ሎሌነት ከመማቀቅ አንድ ቀን ነፃ ሆኖ መኖር ይሻላል

በወያኔ ግፈኛ ስርአት መከራቸውን ከሚያዩ ዜጎች ውስጥ ራሱ ሥርአቱ ለራሱ መገልገያ የሰበሰባቸውና ያሰማራቸው ዜጎች ይገኙበታል። ከእጅ ወደ አፍ እንኳን ለማትሆን ደመዎዝ በሰራዊቱ ውስጥ በተራ ወታደርነትና በበታች ሹማምንት የሲኦልና የጉስቅልና ኖሮ እንደሚኖሩ እናውቃለን።

በየዞኑና በየወረዳው በካድሬነት ወያኔ ለገላጋይነት ያሰማራቸው ሰራተኞችና የድርጅቱ አባሎች ከህዝቡ የጥላቻ ሰለባነት ባልተናነሰ በኑሮአቸው ለራሳቸውም ለቤተሰቦቻቸውም ሳያልፍላቸው እንደሚኖሩ እናውቃለን።

ይልቁንስ የወያኔው የአመራር ጉጅሌ ነገ የት እንደሚያደርሳቸው በማያውቁት ጨለማ ውስጥ ነው የሚዳክሩት ሚስጥርና የዳጎሰ ጥቅም ከነሱ ዘንድ አይደርስም። በቀድሞ ጊዜ የነበሩት የባላባት ሎሌዎች እንኳን ክብር አላቸው።

በዚህ ላይ ሁሉም አስተማማኝ ሎሌ መሆኑን ወያኔ ለማረጋገጫ የሚጠቀምበት ግምገማ አለ። የወያኔ ግምገማ የበታች አባላትና ደጋፊዎቹን በማስፈራራት ያላቋረጠ ድጋፍ እንዲሰጡት የሚያደርግበት በመሰረቱ ከውሻ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የማይለይ ተቋም ነው። የትምህርት እድል የስራ እድገትና የደመወዝ ጭማሪ የወያኔው ጉጅሌ የባርነት መደለያዎች ናቸው።

ግንቦት 7 ከጥቂት ከመንገዳቸው እያወጡ ህዝብ ከሚያሰቃዩት የወያኔ ታዛዥ ሎሌዎች በቀር የሀገርና የወገን ጠላት ናቸው ብሎ አያምንም። ትግላችን ለነሱም ነጻነት ነው። እነዚህ ወገኖቻችን ባገኙት አጋጣሚና እድል ሁሉ ትግሉን ያግዛሉ ብሎም ያምናል። የሚያግዙም አሉ። እርግጥ ነው ባሸከርነት ኑሮ የተንገፈገፉ የሰራዊቱ አባላትና ለህሊናቸው ክብር ያላቸው በርካታ የስርአቱ አገልጋዮች ትግላችንን እየተቀላቀሉ ነው።

ግንቦት 7 ንቅናቄ ዛሬም እንደሁሌው ለነዚህ ወገኖች ኑ ተቀላቀሉን የሚል ጥሪውን ያቀርባል። ሁላችንም ከነክብራችን ሆነን ሰዎችን ሳይሆን ውዲቱን ሀገራችንና ህዝባችንን በፈቃደኝነት በነጻነት የምናገለግልበት ጊዜ እየቀረበ ነው፡፡

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የአንድነት ፓርቲ የስራ አመራር አባል በወያኔ ቅጥረኞች ታግተዉ መደብደባቸዉ ተሰማ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በቅርቡ በመላዉ አገሪቱ ባካሄደዉ "የሚሊዮኖች ድምጽ" ዘመቻ ዉስጥ ከከተማ ወደ ከተማ በመዘዋወር ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረጉትና የፓርቲዉ የብሄራዊ ምክር ቤት አባል የሆኑት መምህር አበበ አካሉ ባሳለፍነዉ ሳምንት ዉስጥ የደህንነት መስሪያ ቤት አባላት ነን ባሉ ሶስት ቅጥረኞች ታግተዉ ክፉኛ እንደተደበደቡና የግድያ ማስፈራሪያም እንደደረሰባቸዉ ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዘገበ። አቶ አበበ አካሉ የደረሰባቸዉን ድብደባ አስመልክተዉ ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ እንደተናገሩት በምሳ ሰዓት ኮተቤ መሳለሚያ አካባቢ ለስራ ጉዳይ ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወሩ ህገ ወጦቹ የወያኔ ደህንነት አባላት በላንድክሩዘር መኪና ተከትለዋቸዉ መንገድ ከዘጉባቸዉ አቶ አበበን በግድ መኪናወ ዉስጥ እንዲገቡ በማድረግ ወዳልታወቀ ቦታ ወስደዋቸዉ ደርቅ ሲሚንቶ ላይ አስተኝተዉ እንደደበደቧቸዉ ተናግረዋል።

ወንለኞቹ የወያኔ ቅጥረኞች መምህር አበበን ከቀኑ 6፡30 እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት ድረስ ሽጉጥ ደግነውባቸው የማያውቁትን የአልኮል ቃና ያለው ፈሻሽ ነገር በግድ በመጋት ከሲሚንቶ ጋር አጣብቀው በተደጋጋሚ የረገጧቸዉ ሲሆን በሰላማዊ መንገድ የሚያካሂዱትን ትግል እስካላቆሙ ድረስ መንግስትን በሀይል ለማውረድ እየሰራህ ነዉ በሚል የሽብርተኝነት ወንጀል እንደሚወነጅሏቸው ከነገሯቸዉ በኋላ እንደለቀቋቸዉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ባለትዳርና የሶስት ልጆች አባት የሆኑት መምህር አበበ አካሉ በአሁኑ ወቅት በመኖሪያ ቤታቸው ተኝተው በማገገም ላይ እንደሚገኙ ፍኖተ ነጻነት ጨምሮ ገልጿል።

## የኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ አሁንም ዉኃ እንደጠማት ነዉ

የወያኔ አገዛዝና የአዲስ አበባ አስተዳደር የከተማዋ የውሃ ሽፋን ከ94 በመቶ በላይ ነዉ እያሉ ቢለፍፉም በአሁኑ ወቅት መሃል አዲስ አበባን ጨምሮ አብዛኛው የአዲስ አበባ ክፍል ከ40 በመቶ የበለጠ የዉኃ አገልግሎት እንደማያገኝ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ደምጽ ዘጋቢዎች ዉስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። የከተማዋ የውሃ ሽፋን እያደገ መጥቷል የሚለዉ የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለሰልጣን ውሃን በቁጠባ የመጠቀም ልምድ ባለመዳበሩ እስከ40 በመቶ የሚደርስ ከፍተኛ የዉኃ ብክነት በከተማዋ ውስጥ አለ በማለት ስር የሰደደዉን የአዲስ አበባን የዉኃ ችግር በነዋሪዎች ላይ ለማሳበብ ሞክሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋን የውሃ እጥረት ለመቅረፍ በ2006 በጀት ዓመት 6 ቢሊየን ብር ገንዘብ የመደበ ሲሆን ይህ ገንዘብ በቀን 110 ሺ ሜትር ኪዩብ የነበረውን የአዲስ አበባን የዉኃ ስርጭት ወደ 210 ሺህ ያሳድገዋል ተብሎ ይጠበቃል። በተለያዩ የአዲስአበባ አካባቢዎች በየዕለቱ የመጠጥ ውሃ በአግባቡ የሚሰራጭ ባለመሆኑ ሰዎች ስራቸውን በመተው ጭምር ውሃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ሲንከራተቱና ለውሃ ማጓጓዣ ከፍተኛ ወጪ ሲያወጡ ማየት የተለመደ ሆኖአል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎችም ውሃ በለሊት ይመጣል በሚል በርካታ ቤተሰቦች ውሃ በመጠባበቅ እንቅልፍ ሳይተኙ የሚያድሩበት ሁኔታ መኖሩ ይታወቃል።

## ወያኔ የሰሜን ዕዝና የአየር ኃይል ዋና አዛዦችን በወዘ

ከ1990ዎቹ የኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ግዜ ጀምሮ በሽግሽጉ መሠረት ኢትዮጵያን ከወረረች ጀምሮ የሰሜን ዕዝ ዋና አዛዥ በመሆን ሲያገለግል የነበረዉ ሌፍተናንት ጄኔራል ሰአረ መኮንንና ለረጂም ግዜ የኢትዮጵያን አየር ኃይል በዋና አዛዥነት የመራዉ ሜጀር ጄኔራል ሞላ ኃይለ ማርያም ከቦታቸዉ ተነስተዉ በምትካቸዉ ሜጀር ጄኔራል ዮሐንስ ወልደ ጊዮርጊስና ሜጀር ጄኔራል አደም መሐመድ የተተኩ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የመከላከያ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ሌፍተናንት ጄኔራል ሰአረ ኮንንና ሜጀር ጄኔራል ሞላ ኃይለ ማርያም ወደ ተሻላና ላቅ ወዳለ የኃላፊነት ቦታ ላይ እንዲቀመጡ ተደርጓል ከመባሉ ዉጭ አዲስ ሀላፊነታቸዉ ምን እንደሆነና ዬትኛዉ መዋቅር ላይ እንደተቀመጡ የተሰጠ ምንም መረጃ አለመኖሩን ምንጮቻችን አክለዉ ገልጸዋል;አዲሱ የአየር ኃይል ሹም ሜጀር ጄኔራል አደም መከላከያ ሚኒስቴር ዉስጥ የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ የነበረና እንዲሁም በአየር ኃይሉ ዉስጥ በአብራሪነት ያገለገለ ሲሆን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን በሚወዛገቡባት የአቢዬ ግዛት የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል ምክትል አዛዥ የነበረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ላለፉት አሥር ዓመታትና በአሁንም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆነዉ አስመላሽ ወልደ ሥላሴ፣ የጠቅላይ ማኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የሕግና ፍትሕ አስተዳደር አማካሪ ሚኒስትር ዴኤታ በመሆን መሾሙ ታዉቋል፡፡ አስመላሽ ወልደ ሥላሴ ፓርላማዉ ዉስጥ ለበርካታ አመታት የፓርላማዉ የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ያገለገለ ሲሆን ኮሚቴዉ ለፓርላማው የሚቀርቡ ረቂቅ ሕጎችን በተለይም ሕግና አስተዳደርን የተመለከቱትን በዋናነት የሚመለከት ሲሆን፣ የአገሪቱ የሕግና የፍትሕ ሥርዓት የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማትንም የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለው፡፡ በቅርቡ ቦታዉን አትመጥንም ተብሎ ከኃላፊነት ቦታዉ የተነሳዉ የፍትሕ ሚኒስትሩ ብርሃን ኃይሉ ከመሰናበቱ አንድ ቀን በፊት ለፓርላማው ያቀረበዉን ሪፖርት በመተቸትና የሚኒስቴሩን ጉድለቶች በማስረዳት እንዲያስተካክሉ መመሪያ የሰጠዉ አስመላሽ ወልደስላሴ መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም።

## የወያኔ ፍትሻ ባህርዳርንና . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የወጣቶች እንቅስቃሴ ለማፈንና አባላቱን ለመግደል የታቀደ እንደሆነ ገልጸዋል። ዊኪሊክስ የተባለዉ ሚስጢር አጋላጭ ድርጅት የዛሬ ሁለት አመት ይፋ ያደረገው መረጃ በግልጽ እንዳሳየዉ የአሜሪካ ኢምባሲ የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ የሽብር አደጋ አለ ለማስባል ሆን ብሎ ፍንዳታዎችን ያቀናብራል ብሎ እንደሚያምን መግለጹ ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በባህርዳር አንድ የባጃጅ ሹፌር በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሎ ተገኝቷል። በወጣትነት እድሜ ክልል የሚገኘዉና የቀበሌ 7 ነዋሪ የሆነው ይህ ወጣት በከፍተኛ ሁኔታ የተደበደበ ከመሆኑም በላይ ሁለት አይኖቹ በአሳቃቂ ሁኔታ ወጥተዉ ከተጣለበት ቦታ ከሁለት ቀ አይኖቹ ወጥተው ከቀናት በሁዋን በኋላ ነው በፍለጋ የተገኘዉ። ኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን በግድያዉ ዙሪያ የባህርዳርን ፖሊስ ኮሚሽን ለማናገር ያደረገዉ ሙከራ እንዳልተሳካ ለማወቅ ተችሏል።

## ደብረማርቆ ዩኒቨርስቲ ዉስጥ ለተነሳዉ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዉስጥ የተነሳዉ የተማሪዎች አመጽ ምክንያቱ አሰገዳጅ ህጉና የምግብ ማነስ ሳይሆን ኢሳትና ሌሎች ሃይሎች ያደራጁት አመጽ ነዉ ብለዉ መናገራቸዉ ብዙዎችን አስገርሟል።ይህንን የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዚዳንት ኢሳት ላይ የሰነዘሩትን ክስ የሰማ አንድ የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪ አመጽ፤ ተቃዉሞና ህዝባዊ እምቢተኝነት ኢትዮጵያ ዉስጥ በየቦታዉ የሚታይ ከስተት መሆኑ እየታወቀ ፕሬዚዳንታኢን የደብረማርቆሱን አመጽ በኢሳት ላይ ማሳበባቸዉ የሚያሳየን የአዋቂ አላዋቂነትን ነዉ ብሏል።

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የተቀሰቀሰዉ አመጽ በስድስት ህንጻዎችና በሶስት የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ አምቡላንሶችን ላይ ከፍተኛ አጉዳት ማድረሱ የታወቀ ሲሆን አመጹን ለመቆጣጠር የፌደራል ፖሊስ በወሰደው እርምጃ በተማሪዎች ላይ ድብደባ ፈጽሟል፡፡ ዪዩኒቨርስቲው መሪዎች የአካባቢው ነዋሪዎች ለዩኒቨርሲቲዉ አመጽ ድጋፍ ሰጥተዋል የሚል ስሞታ ያሰሙ ሲሆን ነዋሪዎች በበኩላቸው ተማሪዎች እየራባቸው ሲወድቁ በዝምታ አለመመልከት የዜግነት ግዴታችን ነዉና እርደታ ለመስጠት ተገድደናል ብለዋል።

## ለእንጀራየ ብዬ !!!

**በሬ ሆይ በሬ ሆይ፤**
**ሞኙ በሬ ሆይ፤**
**ሳሩና አየህና ገደሉን ሳታይ፤**
**እልም ካለው ገደል ወደክብን ወይ።**

ዛሬ ዛሬ “ለእንጀራየ ብየ ወይንኩ ለመኖር” የሚሉ አካሎች ቁጥር እና የአስተሳሰባቸው ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።በተለይም ህግን እናስከብራለን ብለው የቆሙ አካሎች “ለእንጀራየ ብዬ ምንም ይሁን ምን የታዘዝኩትን ሳላቅማማ እፈጽማለሁ” የማለታቸው ነገር ከአሳሳቢ በላይም ነው።እነዚህ አካላት ዛሬ መረቅ የበዛበትን ወጥ በእንጀራ ለመጉርስ ሲሉ ነገና ተነገ ወዲያ የሚሆነውን ማየት ተስኗቸዋል። ዛሬ በያዙት ጠመንጃ ንጹሃን ዜጎችን ገድለው የሚበሉት እንጀራ ነገ ከማይወጡበት ገደል ውስጥ ሊከታቸው እንደሚችል ቆም ብለው ማሳብ ይኖርባቸዋል።

የህግ አስፈፃሚ አካላት ከእንጀራቸው በላይ የሚኖሩለት ትልቅ ቁምነገር ቢኖር የህግ የበላይነትን ማስከበር ነው። እነዚህ አካላት ከማንኛውም ተራ ዜጋ ተለይተው ህግን ለማስከበር ቃለ ማሃላ ፈፅመዋል። ይህን ቃለ መሃላ ሲፈጽሙ ዳኛው እና ተመልካቹ ሂሊናቸው ከፍ ሲል አምላክ ካላቸው አምላካቸው እንዲሁም ህዝብ ነው። ከዚህ ቃለ መሃላ በኋላ ህግ አስከባሪዎች በዋናነት የሚኖሩለትም ሆነ የሚሞቱለት ቁም ነገር እንጀራ ሳይሆን የህግ የበላይነት ነው። የምንኖርለትም ሆነ የምንሞትለት ዋናው ቁም ነገር የህግ የበላይነት እንጂ እንጀራ አይደለም ብለው የሚቆሙ የህግ አስከባሪዎች ባሉበት አገር ህግ ተከብሮ ዜጎች በሠላም ተረጋግተው ለመኖር እድሉን ያገኛሉ። ይህ ግን በኢትዮጵያችን እየሆነ አይደለም።

በኢትዮጵያችን የህግ አስከባሪዎች የሚኖሩለትም ሆነ የሚሞቱለት ዋናው ቁም ነገር “እንጀራዬ!” የሚባል ነገር ከሆነ ሃያ ሁለት ዓመት ሆነው።ህወሃት አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያችንን ድርና ማግ ሆነው እንደ አገር ሊያቆሟት የሚችሉ ዋና ዋና ክሮችን ሲበጣጥስ መኖሩ ከማንም የተሰወረ አይደለም። እየተበጣጠሱ ካሉ ክሮች መካከልም እውነትና ፍትህ ይገኙበታል። የህግ አስከባሪ አካላት ከፍትህና ከእውነት ይልቅ ለሚበላና ለሚጠጣ ከንቱ ነገር የበለጠ ትኩረት የሚሰጡ ሆነው እንዲያስቡ የተደረጉ ይመስላል። በዚህ በህወሃት ዘመን ህግን አስከብራለሁ ብሎ የማለ አካል “ለእንጅራ” ብሎ መሃላውን ያፈርስና ፍትህን ያጎድላል። ”ለእንጀራ”ብሎ በሃሰት ይከሰል ዳኛውም ያለ በቂ ማስረጃ ለእንጀራ ብሎ በሃሰት የእድሜ ልክ እስራት ይፈርዳል። በዚህም ዜጎች ይጎዳሉ ቤተሰብም ይፈርሳል።

ለእንጀራ ብሎ የገዛ ወገኑን የሚገድል ትውልድ መፈጠሩ አገሪቷን በእጅጉ የሚጎዳ ቢሆንም ህወሃቶች እንዲህ ያሉ ትውልዶችን መፍጠር በመቻላቸው ተሳክቶልናል ይላሉ ።በአንዲት አገር ውስጥ ፍትህ እና እውነት ከሚበላ ምናምን ነገር አንሳ ከተገኘች ያቺ አገር እንደ ባቢሎን ግንቦች ወድቃ ከመበታተን የሚጠብቃት ምንም ዓይነት ዋስትና የላትም።ኢትዮጵያ እንዲያ ነች። ኢትዮጵያ ውስጥ ነገን ተስፋ አድርጎ እና ተረጋግቶ ለመኖር የሚቻልበት ሁኔታ የለም። እንዲህም በመሆኑ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚሰደድባት አገር ሁና የዓለምን ትኩረት ለመሳብ በቅታለች። ኢትዮጵያችን ከቄስ እስከ ዩንቨርስቲ ፕሮፌሰር፤ ከተማሪ እስከ ገበሬ፤ ከበረንዳ አዳሪው አንቱ እስከ ተባለ ባለ ሙያ ሁሉም በአንድ ላይ የሚሰደዱባት አገር ሁናለች።

ይሄ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ውርደት ነው።ዘረኞቹ ህወሃቶችና በዙሪያው የተሰባሰቡ ዴማጎጎች ግን ይሄን ውረደት ለመረዳት አልቻሉም።

ለእንጀራው ብሎ ኢ-ፍትሃዊ ደርጊትን የሚፈጽም የህግ አስከባሪ አቅመ ቢስ ወገኖቹን ለስደት ይዳርጋል። ይሄ ሁኔታም አገርን ያፈርሳል እንጂ አይገነባም። በፈረሰ አገር ላይ ደግሞ ለእጀራ ተብሎ የሚሠራ ሥራ አይኖርም። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ህግ አስከባሪዎች “እኔ ምን ላድርግ ለእንጀራዬ ብዬ ነው ህገ ወጥ ድርጊት የምፈጽመው” ሲሉ አለማፈራቸው በእጅጉ ያስገርማል። ምን ዓይነት ዘመን ላይ ደረስን ብለንም እንድንጠይቅ እንገደዳለን። እነዚህ ህግ አስከባሪዎች “ለእንጀራየ ስል ፍትህን አጓደልኩ” ማለታቸው በሌላ መልኩ ሲታይ “ለእንጅራየ ስል አገሪቷ እንድትፈርስ እኔም የበኩሌን ሚና ተጫወትኩ” ማለታቸው መሆኑን መገንዘብ እንዳለባቸው ልናሳስባቸው እንወዳለን።

አንድ ህግ በማስከበር ወይንም ደግሞ የአገርን ደህንነት እጠብቃለው ብሎ የቆመ ዜጋ የገዛ ወገኑን በትእዛዝ የሚገድል ከሆነ ከያዘው ብረት በምን እንደሚለይ ራሱን መጠየቅ አለበት። በምንም ዓይነት መለኪያ “አለቃየ ስላዘዘኝ ሰውን ገድያለሁ” ማለት ከፍርድ ነፃ የሚያደርግ አይሆንም።በኢትዮጵያ ውስጥ አገራችሁንና ዜጎቻችሁን ከጥቃት ለመከላከል ቃል ኪዳን ገብታችሁ ስታበቁ የገዛ ወገኖቻችሁን በማስጨነቅ ላይ ያላችሁ የህግ አስከባሪ አካላት ቆም ብላችሁ እንድታስቡ እንመክራችኋለን። የፈጠራችሁ አምላክ ከተሸከማችሁት ብረት ለይቶ ሰው የሚያደርጋችሁን ፈራጅ ሂሊና የሰጣችሁ መሆኑንም ማስታወስ ይኖርባችኋል።

እናንተ ለእንጀራ ብላችሁ በገዛ ወገኖቻችሁ ላይ ኢ-ፍትሃዊ የሆነ ድርጊት ስትፈጽሙ ዜጎች በህግ ላይ እምነት እንዳይኖራችሁ እያደረጋችሁ መሆኑን ልትገነዘቡ ይገባል። በህግ ላይ እምነት ያጣ ዜጋ እጅግ የከፉ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚስችል አቅም ያለው መሆኑንም መረዳት አለባችሁ።

እስኪ “የህግ አስከባሪ” አባላትን እንዲህ ብለን እንጠይቃችሁ ፤

አንድ ወንድ ልጃችሁን ይማርልኝ ብላችሁ ተማሪ ቤት ሰዳችሁታል። ይሄ ብላቴና በትምህርቱ ጎብዞ ወላጆቹን የሚያስመሰግን ሁኗል። እናትም እሰይ ልጄ በርታልኝ እያለች ሃሴት ታደርጋለች። አባትም እንዲህ ነው እንጂ ልጅ እያለ በልጁ ጉብዝና የሚኮራ ሁኗል። ልጁም ከተማሪ ቤት እንደ ወጣ ፈጥኖ ቤቱ የሚደረስ የቤተሰቡ የዓይን ማረፊያ ነው። ከእለታት አንድ ቀን ይሄ ብላቴና በተለመደው ሠዓት አልደረሰም። ቢጠበቅ ቢጠበቅ ድምጹ የሚሰማ አልሆነም። የዓይኖ ማረፊያ የደስታዎ ምንጭ እና የኩራትዎ ምክንያት የሆነው ልጅዎ አሁንም አልመጣም። ነገሩ ያሳስብዎትና ፍለጋ ብለው ሲወጡ ከደጅ የቆመ አንድ ሰው የልጅዎን መገደል ያረድዎታል።የልጅዎ ገዳይ መንግስት የቀጠረው አነጣጥሮ ተኳሽ መሆኑንም ጨምሮ ይረዳሉ።

ልጅዎን ተኩሶ ጭንቅላቱን በርቅሶ የገደለው ህግ አስከባሪ ተብየም “እኔ ምን ላድርግ ለእንጀራየ ስል  የታዘዝኩትን ፈፀምኩ” ማለቱንም ሰሙ።በዚህ ሁኔታ የሚኮሩበትን አንድያ ልጅዎን አጥተው ሃዘን ተቀምጠዋል። በዚህ ግዜ የመንግስቱ ጋዜጦች የእርስዎ ልጅ የተገደለው ባንክ ሊዘረፍ ሲል ነው ብለው ዜና ይዘው ብቅ አሉ። የዚያ የንጹህ ልጅዎ ታሪክ ላይም እውነት ያልሆነ ታሪክ ተጨምሮበት የብላቴናው ፍፃሜ ሆነ። እርስዎም በዚህ ተቆጥተው የልጅዎን ገዳይ ወደ ፍትህ ለማቅረብ ወደ ፍርድ ቤት ይሄዳሉ። እንዲህ በማድረግዎ መንግስት የአገሪቷን ሠላም ለማስጠበቅ የወሰደውን እርምጃ ተቃወሙ ተብለው እጀ ተይዞ ወህኒ ይወረወራሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለ ግፉ ተፈፅሞ አይተናል።በዚህ ሁኔታ የዓይኖቻቸው ማረፊያ የሆኑ ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆች ደጃቸውን ዘግተው የሚያዜሙት የሃዘን እንጉርጉሮ ሰማየ ሰማያቱን ሰንጥቆ እፈጣሪ ደጅ ደርሷል። ሌሎችም አገር አልባነት ተሰምቷቸው “ለመሆኑ ይህች አገር የማን ነች” እያሉ እየጠየቁ ነው። ህወሃቶች ለዚህ ሮሮና ጥያቄ በቂ መልስ የላቸውም። ወደፊትም አይኖራቸውም። እነርሱ አገራቸው ሆዳቸውና እየዘረፉ የሚያከማቹት የገንዘብ ብዛት እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ያላችሁ የፌዴራል ፖሊስ አባላትና የደህንነት ሠራተኞች ይሄ በደል የተፈፀመው በእናንተ ላይ ቢሆን “ለእንጀራየ ብዬ የታዘዝኩትን ፈፅሜያለሁ” ለሚል ህግ አስከባሪ እና እርሱን ለሚያዘው አካል መልሳችሁ ምን ይሆን ?

በመጨረሻም እንዲህ እንላለን።አንድ መንግስት መፍረስ የሚጀምረው ዜጎች እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ ሲጀምሩ ነው።እነዚህ ጥያቄዎች ለአገር መፍረስ ምልክቶች ናቸው።ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ከውዳቂ መንግስታት ተርታ ገብታ ልትቆጠር የበቃችሁ። ኢትዮጵያችንን ለመታደግ የህግ አስከባሪዎች ለህግ የበላይነት እንዲሰሩ እንመክራቸዋለን። ዋስትናችሁ የሚያዛችሁ የጨለማው ንጉስ ህውሃት ሳይሆን ዜጎች በህግ ፊት በእውነት በፍትህ እና በእኩልነት መዳኘት መቻላቸው ነው።ፍትህን ከህወሃት ለሚወረወርላችሁ ፍርፋሪ እንጀራ ብላችሁ ማጓደላችሁን የምትቀጥሉ ከሆነ ፍፃሜያችሁ ከመቸውም ግዜ የከፋ እንደሚሆን አትጠራጠሩ። ፍትህ ማለት እውነት ነች። እውነትም ፍትህ ነች። እነዚህን ሁለት ገፀ በረከቶችን ልሞተ ለእንጀራ ብላችሁ መርገጣችሁን ካላቆማችሁ የሰደታችሁ ዘመን የጠነከርባችኋል።

የጨለማው ንጉስ የህወሃት መሪዎች እንደሆኑ ሁሉን ትተው በዝሪፊያ ላይ ተጠምደዋል።የዘረፉትንም ይዘው የሚሰወሩበትን ሥፍራ እየፈለጉም ነው።እነዚህ ዘረኞች “ካለኛ ጀግና የለም” እያሉ የሚዘባበቱበትና ብዙሃኑን ተጭነው የሚኖሩበት ዘመን በቅርቡ እንደሚያበቃ ልናስታውሳቸው እንወዳለን። ያለምንም ጥርጥር ህውሃት ከህግ በታች የሚሆንበት ግዜ እየመጣ ነው። በዙሪውያውም የተሰባሰቡ ጉግማንጉጎች የጠዋት ፀሃይ እንዳየው ጤዛ መርገፉቸው አይቀርም። እኛም ለዚህ ግብ እየሰራን ነው።

የጨለማው ንጉስ ተወግዶ የነፃነት ጎህ በኢትዮጵያ ላይ ሲያበራ “ለእንጀራየ ስል ታዝዤ ንጹሃን ዜጎችን ገደልኩ” ማለት መልስ አይሆንም።የህግ አስከባሪዎች ሆይ ስሙ ! አልመሸም። አሁንም በቂ ግዜ  አለ።ፍትህን፤ እኩልነትን እና ነፃነትን በኢትዮጵያ ለማንገስ በሚደረገው ትግል ውስጥ ተቀላቀሉ።ብትወድቁ የሚያነሳችሁ፤ መሸሸጊያ ብትሹ መደበቂያ የሚሆናችሁ ህዝብ እንጂ ዘረኞቹና ዘራፊዎቹ ህውሃቶች አይደሉም። እነሱማ እንደ ሸንኮራ መጥጠው ይተፏችኋል እንጂ መድህን አይሆኗችሁምና አሁኑኑ ከህዛባዊ ትግሉ ግን እንድትቆሙ ደግመን ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አመታት ከ400 ሺ በላይ ዜጎቿን በስደት አጣች

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በህዝብና በአገር ላይ የሚፈጽመዉን ግፍና በደል በመሸሽ ከኢትዮጵያን እየጣለ የሚሰደደዉ ሰዉ ቁጥር ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ መምጣቱን ከአገር ዉስጥና ከአለም አቀፍ ተቋሞች የሚመጡ መራዎች ጠቆሙ። በቅርቡ ከወያኔዉ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ባለፉት 2 ዓመታት ዉስጥ ብቻ ከ400 ሺ በላይ ዜጎች ኢትዮጵያን ለቅቀዉ መሰደዳቸዉ ታዉቋል። ይህንን እጅግ በጣም አሳሳቢ መረጃ ይፋ ያደረገዉ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ ጨምሮ እንዳስረዳዉ ይህ ቁጥር የወያኔን ጫናና መከራ ላለማየት በህጋዊ መንግድ አገር እየለቀቁ የሚሄዱትን ሰዎች እንደማይጨምር ታዉቋል።

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ኢትዮጵያዉያን ከደርግ ዘመን ጀምሮ በጎንደር፤ በሐረር፤በወለጋ፤ በባሌና በሲዳሞ በኩል አገር እየጣሉ እንደሚሰደዱ የታወቀ ሲሆን ወያኔ አትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ የአገሪቱ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሁኔታ ይሻሻላል በሚል ብዙዎች ኢትዮጵያን እየለቀቀ የሚሰደደዉ ሰዉ ቁጥር ይቀንሳል የሚል እምነት ነበራቸዉ። ሆኖም ወያኔ ብዙም ሳይቆይ የዘረኝነት ፖሊሲዉን ተግባራዊ ማድረግ በመጀመሩ የስደተኛዉ ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣቱ ታዉቋል። በደርግ ዘመን በብዛት ይሰደድ የነበረዉ የቀይ ሽብር ብትር ያርፍበት የነበረዉ ወጣቱና ምሁሩ ሲሆን ዛሬ በወያኔ ዘመን ግን ወንድና ሴት ሳይለይ ወጣቱ፤ተማሪዉ፤ ምሁሩ ፤ሰራተኛዉና ገበሬዉ አንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የአለማችን አምስተኛዉ ታዳጊ ኤኮኖሚ ነዉ እያሉ ወያኔና አፈ ቀላጤዎቹ ቢናገሩም ዛሬም ኢትዮጵያ አፍሪካ ዉስጥ ከፍተኛ ህዝብ የሚሰደድባት አገር አንደሆነችና በተለይ በከፍተኛ ደረጃ የተማረዉን የሰዉ ኃይል በተመለከተ ኢትዮጵያ ምሁሮቻቸዉን በአዉሮፓና በአሜሪካ ከተቀሙ ታዳጊ አገሮች ግንባር ቀደሚ እንደሆነች አለም አቀፍ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በተለይ የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ስራ ፍለጋ ወደ ፋርስ በህረሰላጤ አገሮችና ወደ መካከለኛዉ ምስራቅኢ አገሮች የሚሄዱ ኢትዮጵያዉያን ሴቶች ቁጥር በከፈተኛ ፍጥነት ማደጉ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህንኑ ተከትሎ አያሌ የዜጎች ወደነዚህ አገሮች የሚያደርጉትን ፍልሰት የሚያፋጥኑ ድርጅቶች አዲስ አበባን ማጨናነቃቸዉ ይታወቀቃል። ወያኔ አገዛዝም ቢሆን በዚህ የሰዉ ልጆች ንግድ ተጠቃሚ ስለሆነ ስራ ፈላጊዎች ከመሰደድ ይልቅ አገር ዉስጥ ስራ እንዲያገኙ ያደረገዉ ምንም ነገር የለም። አርብ አገር የሚሄዱ ኢትዮጵያዉያን ሴቶች የሚደርስባቸዉ ከፈተኛ ችግር፤ ሞትና እንግልት በአለም አቀፍ ሜድያዎች ጭምር በመዘገቡ ወያኔ በቅርቡ ለስራ በሚል ወደ ውጪ በሚጓዙት ላይ እገዳ መጣሉ ይታወቃል።

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ አበበ ሀይሌ እንዳሉት፥ እገዳው ከተጣለባቸው ሀገራት መካከል ሊባኖስ ፣ ኳታር፣ ሳውዲ አረብያ፣ ኩዌት፣ የመን፣ ሱዳንና ደቡብ አፍሪካ ይገኙበታል።በእገዳው መሰረት ካሁን ቀደም ቪዛ ያገኙትን ጨምሮ ቪዛ ለማግኘት እየተጣጣሩ ያሉትም ቢሆን ወደ ሀገራቱ መጓዝ አይችሉም።፤ እገዳው በቤት ሰራተኝነት ተቀጥሮ ለመስራት ከሚደረጉት ጉዞዎች ባሻገር አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ባላቸው ሙያዎች ላይ የሚደረጉ ጉዞዎችን እንደማይመለከትም ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። በመንገድ የቀረው ቀርቶ ወደ መጨረሻ መዳረሻ ሀገር የገቡት ዜጎች እጣ ፈንታ አብዛኛውን ጊዜ ስቃይና እንግልት ቢሆንም ፥ ዛሬም በዚያ የሞት ጎዳና ላይ የሚተሙ ዜጎች ቁጥር ሊቀንስ አልቻለም።

### የአዲስ አበባ አገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ ተሰደዱ -ሲኖዶሱ ያሳለፈዉን ዉሳኔ ፓትሪያሪኩ ቀለበሱት

በቅርቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አመታዊ ጉባኤውን ባካሄደበት ወቅት የአዲስ አበባን ሃገረ ስብከት ወክለዉ በጉባኤዉ ላይ የተገኙትና ከፓትሪያሪኩ ጋር እንደማይስማሙ የሚነገርላቸዉ መጋቤ አዲስ ይልማ ቸርነት ለስደት መዳረጋቸዉንና ምክትላቸው የነበሩት አቶ ዩናስም ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ መደረጉን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ። የሲኖዶሱ ስብሰባ ከመጀመሩ አስቀድሞ የፌደራል መንግስት ጉዳዩች ሚኒስትር ተወካዩች በተገኙበት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰዎች፣የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎችና ጳጳሳት በተገኙበት በተካሄደ ውይይት ጳጳሳቱ የመንግስት ተወካዮች ላቀረቡት ሐሳብ ያላቸውን ልዩነት በመግለጽ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ እጁን እንዲሰበስብና ለህገ መንግስቱ ተገዢ እንዲሆን መጠየቃቸው ይታወሳል።

ቅዱስ ሲኖዶሱ በዚህ ሳምንት ዉስጥ በደረገዉ ስብሰባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሊቀ ጳጳስ የሆኑት አቡነ እስጢፋኖስ ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ በአብላጫ ድምጽ የወሰነባቸዉ ፓትርያርኩ አቡነ ማቲያስ አዲስ አበባ የእኔ ልዩ ሐገረ ስብከት በመሆኑና ማንም ሊያዝበት ስለማይችል ሊቀ ጳጳሱ በቦታቸው እንዲቀጥሉ በመወሰን የትናንቱን ናትና ማንም ሊያዝዝባት አይችልም በማለት የቅዱስ ሲኖዶሱን ዉሳኔ መሻራቸዉ ታወቀ። የሲኖዶሱ ገባኤ ለአንድ ሳምንት ያክል የቀጠለ ሲሆን ሹም ሽሩንና የፓትሪያሪኩን ዉሳኔ ጋዜጠኞች ይዘግቡታል በሚል ፍራቻ ሲኖዶሱ ለጋዜጠኞች ወደ ስብሰባው የመግቢያ ፈቃድ ከልክሏል።፡

## በደቡብ ክልል የመምህራን ተቃውሞ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በስፍራው ተገኝተው መምህራኑን ለማግባባት የሞከሩ ቢሆንም መምህራኑ ግን ያለፈቃዳችን ቆርጣችሁ የወሰዳችሁትን ደሞዛችንን መልሳችሁ እስካልሰጣችሁን ድረስ ከእናንተ ጋር ለመወያየት ፈቃደኛ አይደለንም የሚል መልስ መስጠታቸዉ ታዉቋል።

ከወረዳዉ በየቀኑ የሚደርሰን ዜና እንደሚያመለክተዉ የወረዳዉ ባለስልጣኖች መምህራኑን አመጹን ካቆማችሁ የተቀረጠባችሁ የመስከረም ወር ደሞዝ ይመለስላችኋል፤ የጥቅምት ወር ደሞዝም ያለ ፈቃዳችሁ አይቆረጥባችሁም እያሉ ይቅርታ በመጠየቅ ጭምር ለማግባባት ቢሞክሩም፤ ስለአባይ ግድብ ከእናንተ የተሻለ በቂ መረጃ አለን ያሉት መምህራን የባለስልጣናቱን የልመና ጥያቄ ውድቅ አድርገዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ከምእራብ አባያ መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 15 የኢህአዴግ አባላት የሆኑ መምህራን ከድርጅት አባልነት ለመሰናበት የመልቀቂያ ደብዳቤ አስገብተዋል። መምህራኑ ድርጅቱን ለመልቀቅ ካቀረቧቸው መከንያቶች መካከል የኢኮኖሚ ችግር፣ የድርጅቱ ኢ- ዲሞክራሲያዊ ባህሪና በየጊዜው የሚፈጠርውን ጫና ለመቋቋም አለመቻል የሚሉ ይገኙበታል። ቀድሞ ብሎ በመሰናዶ ትምህርት ቤቱ ውስጥ 75 የኢህአዴግ አባላት መምህራን የነበሩ ሲሆን፣ 47 መምህራን ድርጅቱን በመልቀቃቸው 28 አባላት ብቻ ቀርተው ነበር። ከ28ቱ መምህራን መካከል ደግሞ ካለፈው ሰኞ ጀምሮ 15ቱ መምህራን የመልቀቂያ ደብዳቤ አስገብተዋል።

## ዝምታ ይነቅዛል

ብሂል ብሎ ሞቶ - ተደንቅለት ሃረግ ቋጭቶ
አፉን ለጉሞ ዘግቶ - ሂሊናዉን አሽጎ
ዉርደት ጥቃትን ተመልክቶ - ሰምቶ እንዳልሰማ
ግዜ ሰጥቶ
ራስ ማሳዉን አግሎ - ለቀፈቱ ተነጥፎ
አለዚያም ተርበትብቶ - ለማይቀረዉ ሞቱ ርዶ
ያበላሻል ተበላሽቶ - “ዝም አይነቅዝም”ን ተቀኝቶ።

ማነዉ የተረተዉ “ዝም አይነቅዝም” ያለዉ?
ሀሰት ነዉ፡ !! ዝምታ ይነቅዛል !!
ቅን ቅን ይበላና አፈር ትቢያ ያደርጋል።
ግፍን ዝም ካሉት ታቅፈዉ ከቻሉት
ሆድ ይቻለዉ ብለዉ ሆድ ውስጥ ከቀበሩት
በ “ቀን ይፍጀዉ” ስሜት ካቀረቀሩለት
ተንቀጥቅጠዉ ፈርተዉ ጎብጠዉ ከሄዱለት
አቦ ተናገሩ ዝምታ ዝምታ ይገድላል
. . .ዝምታ ያበግናል
ሰዉነት ያቆስላል ሰዉነት ያንድላል
ጥበት ሲያስጨንቀን - ትምክህት ሲያለፋን
አይኑን በጨዉ አጥቦ- ገዳይ አዳኝ ነኝ ሲል
የምን ዝም በሉ- የምን ተዉ እረፉ
እግርና እጅ ዘርግቶ - ለጅብ እያስበሉ
ተኙ ብሎ መንገር - ሚስጥር ዝም በሉ
አቦ ተናገሩ ዝምታ ዝምታ ይገድላል
. . .ዝምታ ያበግናል
መርዝ ነዉ ዝምታ - አገር ይበክላል
እምቅ አርገዉ ይዘዉ በሆድ ካዋሉትም
ከፉ ነዉ ዝምታ ዕድሜ ያሳጥራል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org